HUH HOWARD UNIVERSITY HOSPITAL

# የጨጓራና አንጀት ሕክምና ክፍል
# (Division of Gastroenterology)

## የጨጓራ ምርመራ (Upper Endoscopy) ዝግጅት መመሪያዎች

### መመሪያ 1:- የመድሃኒት አወሳሰድ መመሪያዎች

**የደም ማቅጠኛዎችን እየወሰዱ ከሆነ**

- Xarelto®፣ Eliquis®:- ምርመራው ከመደረጉ ከ3 ቀናት በፊት ያቁሙ።
- Plavix (ፕላቪክስ)® ምርመራው ከመደረጉ ከ5 ቀናት በፊትያቁሙ።
- Warfarin (Coumadin®)፣ ምርመራው ከመደረጉ ከ3 ቀናት በፊት ያቁሙ።

**ኢንሱሊን እየወሰዱ ከሆኑ**

- አጭር ጊዜ የሚቆይ ኢንሱሊን:- ይህን በፍጹም በምርመራው ቀን አይውሰዱ።
- ረጅም ጊዜ የሚቆይ ኢንሱሊን:- ምርመራው ከመደረጉ በፊት ባለው ምሽት የሚወስዱትን መደበኛ መጠን ግማሹን ብቻ ይውሰዱ።

**የ GLP-1 አጎኒስት (Agonists) መድኃኒቶችን የሚወስዱ ከሆነ (ለስኳር ህመም ወይም ለክብደት መቀነስ የሚያገለግሉ)**

- በመርፌ የሚወሰዱ (ለምሳሌ:- ኦዜምፒክ (Ozempic)®፣ ዌጎቪ (Wegovy)®፣ ትሩሊሲቲ (Trulicity)®ዜፕባውንድ (Zepbound)®፣ ቢሳይዝ (BCise)® እና ሙንጃሮ (Mounjaro)®):- ምርመራው ከመደረጉ ከ1 ሳምንት በፊት ያቁሙ።
- በአፍ የሚወሰዱ (ለምሳሌ:- ቪክቶዛ (Victoza)®፣ ሳክሴንዳ (Saxenda)®ባዬታ (Byetta)®እና አድሊክሲን (Adlyxin)®):- ምርመራው ከመደረጉ ከ24 ሰዓታት በፊት ያቁሙ።

### መመሪያ 2:- ምርመራው ከመደረጉ በፊት ባለው ምሽት

- ቀለል ያለ እራት ይመገቡ

### መመሪያ 3:- ምርመራው በሚደረግበት ቀን

- ከእኩለ ሌሊት በኋላ ምንም ዓይነት ምግብ አይብሉ ወይም ፈሳሽ አይጠጡ።
- ሌላ መመሪያ ካልተሰጠዎት በስተቀር፣ አስፈላጊ የሆኑ የጠዋት መድኃኒቶችን (እንደ የደም ግፊት፣ የታይሮይድ፣ የሚጥል በሽታ እና የልብ መድኃኒቶች) በጥቂት ውሃ መውሰድ ይችላሉ።
- ምርመራው በሚደረግበት ቀን ጠዋት ምንም ዓይነት በአፍ የሚወሰዱ የስኳር መድኃኒቶችን አይውሰዱ።
- ምቹ ልብስ ይልበሱ እና ውድ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይዘው አይምጡ።

### ያስታውሱ:-

- መታወቂያዎን፣ የኢንሹራንስ ካርድዎን እና የሚወስዷቸውን መድኃኒቶች ዝርዝር ይዘው ይምጡ።
- ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው አብሮዎት መምጣት ያለበት ሲሆን፣ ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ቤት ሊወስድዎት ዝግጁ መሆን አለበት።

ማንኛውም ጥያቄ ወይም የሚያሳስብዎት ነገር ካለ፣ እባክዎ የጨጓራና አንጀት ሕክምና ክፍልን (Gastroenterology Department) በ 202865- 1374 ከጠዋቱ 9:30 AM እስከ ከሰዓት 4:30 PM ባለው ጊዜ ውስጥ ያነጋግሩ። ከሥራ ሰዓት ውጭ ለሚደረግ እርዳታ:- በ 202-865-6100 በመደወል በሥራ ላይ ያለውን የጨጓራና አንጀት ስፔሻሊስት (GI) እንዲያገናኙዎት ይጠይቁ። እነሱም የሚያሳስብዎትን ጉዳይ ሊፈቱልዎት ይችላሉ።